# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) 36ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን አከበረ




የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) 36ኛ ዓመት የምስረታ በዓል፣ ጀርመን ሀገር፣ ፍራንክፈርት ከተማ ውስጥ፣ ነሐሴ 24 ቀን 2000 ዓ. ም. በተካሄደ ከፍተኛ ሕዝባዊ ስብሰባ ተከብሮ ውሏል። በዝግጅቱም ላይ ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ አባላቱ፣ ደጋፊዎቹና በከተማው የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተዋል።






በኢሕአፓ የረጅም ዓመታት አኩሪ የትግል ታሪክ ክቡር የሕይወት ዋጋ እና ሌላም መስዋዕትነት የከፈሉ ጀግኖችንና ሌሎችንም ሕዝባዊ ሰማዕታት ለማሰብ ለአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት በማድረግ ነበር ሕዝባዊ ስብሰባው የተጀመረው። በማስከተልም በአውሮፓ የኢሕአፓ አህጉራዊ ኮሚቴ፣ የበዓሉ ዝግጅት አስተባባሪ ተጠሪ የዕለቱን እንግዶችና ታዳሚዎች እንኳዋን ደህና መጣችሁ ከአሉ በሁዋላ ወደ መድረኩ የጋበዙት፣ ከጀርመን የኢሕአፓ ድጋፍ ኮሚቴ አባላት ውስጥ መዘምራንን ነበር። ወጣቶቹ፡

ለዘመናት በጭቆና ማጥ
በግፍ ሰንሰለት ታስሬ



መብቴን ላስከብር
ጨቋኝን ልሽር
ተነሽቻለሁ ዛሬ...

በማለት የኢሕአፓን መሪ መዝሙር «ለትግሉ ነው ሕይወቴ»ን ሲዘምሩ ላዳመጠ እና ላስተዋለ፣ ምንም እንኳዋን በኢሕአፓ ላይ ፋሽስቶች ያደረሱት ጭፍጨፋ እያንዳንዱን ቤት ያንኩዋኩዋ፣ ዕልፍ አዕላፋትን የመተረ ቢሆንም፣ ሰማዕታቱ የወደቁለትን ክቡር ዓላማ ወራሽ እንዳላሳጣው መዘምራኑ እራሳቸው ምስክር ይሆኑታል። የሚበዛው ታዳሚ ወጣት መሆኑንን ላስተዋለም ይከው ነው የሚታየው።





በማስከተልም የእለቱ እንግዶች ማለትም:

ከኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ስለፓርቲው ታሪክ፣ ስለሀገራችንና ስለዓለም ወቅታዊ ሁኔታ አጭር ማብራሪያ ሰጥተዋል። ኢትዮጵያዊያን ኢትዮጵያን የምንታደጋት በራሳችን ቆመን፣ ወገንንና ጠላትን ለይተን ለስርዓት ለውጥ ስንታገል እንጅ «ወያኔ ኢትዮጵያን ሊያጠፋት ነው!» ስንላቸው በሆዳቸው «ምነው ባደረገው!» የሚሉትን ባዕዳን ሃይሎች በመማጠን አለዚያም ከኢትዮጵያዊነት እስከወዳኛው የተጣሉትንና የነኘሁ የውጭ ሃይላት ጥቅም አስጠባቂ የሆኑትን የወያኔ መሪዎች በመለማመጥ እንዳልሆነ አስገንዝበዋል።



ሌላዋ ተጋባዥ እንግዳ ደግሞ የዓለምቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ) አመራር አባል ወይዘሮ አስቴር ደመቀ ነበሩ። እሳቸውም ስለድርጅታቸው ዓማና እንቅስቃሴ አጭር ማብራሪያ ስጥተዋል። ዓኢሴድ ከማንኛቸውም የኢትዮጵያን አንድነት እና የሕዝቡዋን የዴሞክራሲ መብቶች ለማስከበር ከሚታገሉ ሃይሎች ጎን የመቆም መርህ የሚያራምድ እንደመሆኑ ለኢሕአፓም ያላቸውን የትግል አጋርነት ጠቅሰው «እንኳዋን አደረሳችሁ» በማለት መልካም ምኞታቸውን ገልፀዋል።

ሶስተኛዋ እንግዳ ወይዘሮ ገነት ግርማ ደግሞ ከወጣትነታቸው አንስቶ አሁንም ድረስ ባለፉበት ረጅም የትግል ተመክሮ ላይ በመመርኮዝ ትምህራታዊ ማብራሪያ አቅርበዋል። በዚሁ ማብራሪቸውም ተሰደን የምንኖርባቸው ሀገሮች እውን አድርገውት ያለው ዴሞክራዊ ስርዓት የተገኘው በትግል መሆኑን አስታውሰዋል። ኢሕአፓም ተደራጅቶ የመታገልን አስፈላጊነት በመገንዘብ ከ36 ዓመት በፊት ተመስርቶ ፈር ቀዳጅ (የመጀመሪያው) የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን አስገንዝበዋል።

በእንግዶቹ ከተሰጠው ማብራሪያና ከተከተለው ውይይት በተጨማሪ የፓርቲውን መራራ ትግል የሚያሳዩ የድምፅና ምስል ቅንብሮች እና የህትመት ውጤቶች ለዕይታና ለሺያጭ ቀርበዋል።



የፖለቲካ፡ ፓርቲዎች
ይፈቀዱ።
የጸሐፊ፡ ልጅ፡
ይማር።





EPRP
EPRA
MIT DEM
STISCHEN
RROR!
ES LEBE DIE
EPRP


ቀይ ሽብር




ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ የተከሰተውን ሕዝባዊ ትግልና የተከፈለውን መስዋዕትነት የሚዘክሩ ፎቶዎችም ለዕይታ ተለጥፈው ነበር።

በመሃል በመሃሉም ታዋቂው የጥበብ ሰው ዓሊ ሁሴንም የተለያዩ ቀስቃሽ ግጥሞችንና በፓርቲው የትግል ታሪክ በፅናት ቆመው የወደቁ ሰማዕታትን ዕውነተኛ ገድሎች ከትውስታቸው ለታዳሚዎቹ አቅርበዋል። ከኢሕአፓ የሀገር ቤት (ኢትዮጵያ) ክፍል፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሕዝባዊ ትግል በወገናዊነት ከቆሙ የሕዝብ መገናኛ አካላት፣ ከሰማዕታት ቤተሰቦች ወዘተ የተላኩ የእንኳዋን ደስ አላችሁና የአጋርነት መግለጫ መልዕክቶች ተነበዋል።




ከጀርመን የኢሕአፓ ድጋፍ ኮሚቴ አባላትም ሁለት ወጣቶች ለትግል አነሳሽ የሆኑ ግጥሞቻቸውን አንብበዋል። ሕዝባዊው ስብሰባ ከጠናቀቀ በሁዋላም በተከታዩ ዝግጅት ድምፃዊው ኤልያስ ተባባል ታዳሚዎቹን ሲያዝናና አምሽቱዋል። በዚሁ የሙዚቃ ዝግጅትም ላይ ከታዋቂ ዘፈኖቹ በተጨማሪ በሕዝባዊው ትግል የኢሕአፓ ታጋዮች የከፈሉትን መስዋዕትነት፡ ያስተማሩትን ቆራጥነትና ፅናት፡ የዘከረበትን፡ በወያኔ እጅ ወድቀው የደረሱበት ያልታወቀ አባላትን ያወሳበትን አዲስ ዜማ አቅርቡዋል።